በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 4


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መጋቢት ፫ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## እርስ በርስ መግባባት

- አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር የተነጋገረው በርሱ በባሕርይ ልጁ በኩል ነው፡፡ ልጁም በመጀመሪያ የነበረ ከሁሉም በላይ የሆነ ሰውና እግዚአብሔርን ያስታረቀ ቃል ነው፡፡ ‹‹ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፥ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኂለን›› *ቀዳ ዮሐ 1፡1-2፡፡*
- ጌታችንና ቤተ ክርስቲያን … የክርስቲያኖች ሥዕላትም… ዘወትር የሚያነጋግሩን ናቸው፡፡
- ጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብም ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሪያ መንገዶች ናቸው፡፡
- የአርምሞ ጊዜያትም ከራሳችንና ከጌታችን ጋር የምንነጋገርባቸው ናቸው፡፡
- ጌታችንን ማመስገንም ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር መግለጫና መግባቢያ መንገድ ነው፡፡
- አገልግሎትም ሌላው ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር መግለጫና መግባቢያ መንገድ ነው፡፡
- ክርስትና በጌታችንና በሰው፣ በጌታችንና በቤተ ክርስቲያን፣ በሰውና በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በሰውና በሰው መካከል የሚገኝ የማያቋርጥ የፍቅር ግኑኝነት (አግባቦት) ነው፡፡
- በክርስቶስ የሆነ ጋብቻ ከሕይወት ጋር አንድ ለመሆን በሚወስን ሰው የሚፈጸም ሲሆን ይህም በመግባባት ይጀምራል፡፡


# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 4

## እርስ በርስ መግባባት

- በክርስቶስ የሆነ ጋብቻ በማያቋርጥ የርስ በርስ ፍቅር በመግባባት ሥርዓት የሚመራ የተቀደሰ ግኑኝነት ነው።
- በተጋቢዎቹ መካከል ያለው የመግባባት ግኑኝነትም ከቃል ኪዳናቸው በፊት የሚጀምር ሲሆን በቃል ኪዳናቸውም አድጎ በትዳር ሕይወታቸው እየበሰለ እየጠነከረ ይሄዳል።
- ይሁን እንጂ አግባቦት ልጅ ከልጅነቱ ጀምሮ የሚማረው በዕድገት ሂደትም እያደገ ሄዶ ወደ ብስለት የሚደርስ ብቃት ነው። ‹‹መልካም ተግባቢ›› ይሆኑ ዘንድ ራሳቸውን የሚያስተምሩ ሰዎች የተባረኩ ናቸው።

<u>በባልና በሚስት መካከል ያለ መግባባት</u>

- በተጋቢዎች መካከል ያለ ግኑኝነት በሁለት ሰዎች መካከል ያለ ግኑኝነት ብቻ አድርገን ማሰብ አይገባንም። ምክንያቱም ይህ ግኑኝነት ባልን - ሚስትንና - ጌታችን አምላካችን ክርስቶስን የሚገኙበት ነውና። ይህን ካስተዋልንም ለመግባባት የምናደርገውን ጥረት የሚያጠፉብን እንቅፋቶች ሁሉ ይወገዳሉ።



# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4</u>

## እርስ በርስ መግባባት

- ይህን የተቀደሰ ግኑኙነት በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ማጥበቅ የሚጠበቅብንም ለዚሁ ነው፡፡

  1. ዘወትር አብሮ በመጸለይ
  2. ቢያንስ በሳምንት ሁለት ቀን መጽሐፍ ቅዱስን አብሮ ማንበብ (ከሆንልንም በየቀኑ)
  3. ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመገስገስ ቅዳሴ አስቀድሰን ቅዱስ ቁርባንን መቀበል፡፡

***ስኬታማ መግባባት የሚፈጠረው፡-***

- ጥሩ አድማጭ
- መሳሳታችንን አምነን መቀበል ስንችል
- የ‹‹ሌሎችን›› አመለካከት ወይም አስተሳሰብ ስናከብር
- ንግራችንን በፈገግታና (የሰማኒያ ዓመት አረጋዊም ብንሆን) በተረጋጋ መልክ በእጅ እየዳሰስን ስንናገር
- በነጻነት በግልጽ በትሕትና ሆነን ራሳችንን መግለጽ ስንችል
- ለንግግሩ በቂ ጊዜ ለመስጠት ዝግጁ ስንሆን

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## እርስ በርስ መግባባት - በባልና በሚስት መካከል

*ስሌታማ መግባባት የሚፈጠረው፡-*

- ተናጋሪውን በንግግር መካከል ባለማቋረጥ
- የሌላው ሰው ሐሳብ ወይም አቀራረብ ከእኛ ለየት ያለ ሆኖ ሲገኝ መቀበል ስንችል
- ተገቢ ወቀሳና ትችትን መቀበል ስንችል
- ለሌላው ሰው ምልከታ መራር ካልሆን
- የሌላውን ሰው ስሜት፣ ሐሳብና አቀራረብ መረዳት ስንችል
- አዛኝና ነገሮችንም ሆነ ሰዎችን የምንረዳ መሆን
- ንግግሩ በመቀባበልና በፍቅር እንዲጠናቀቅ ተገቢውን ኀሊናዊ ኃላፊነት የምንወጣ መሆን
- ተጋቢዎች ሁለታችን ብቻ በየቀኑ ቢያንስ ለግማሽ ሰዓት ያህል በመቀራረብ መነጋገር የሚያስችለን ዕድል እንዲኖር በመገፋፋት
- በተጨማሪም ተጋቢዎች ብቻ በየሳምንቱ ቢያንስ ለግማሽ ቀን አብራችሁ የምታሳልፉበት ዕድል እንዲኖር ግፊት ማድረግ

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## እርስ በርስ መግባባት - በባልና በሚስት መካከል *አለመግባባትን የሚያሰፍኑ ምክንያቶች*

- የተወደዳችሁ ወንዶችና ሴቶች! በእኛና በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ያለው ግኑኝነት ተጠብቆ እንዲቀጥል የሚከተሉትን ነገሮች ማስወገድ ይጠበቅብናል፡፡
  - ‹‹ሚስቴ እንደምወዳት ወይም ባሌ እንደምወደው ስለምታውቅ/ስለሚያውቅ እወድሻለሁ/እወድሃለሁ ማለት አያስፈልገኝም›› ብለን በማሰብ ነገሮች አቅለን ከመውሰድ እንቆጠብ፡፡
  - ከትዳር አጋራችን ጋር አብረን የምናሳልፈው ጊዜ እስክናጣ ድረስ በውጥረት ውስጥ መሆንን እናስወግድ፡፡ የሁላችንንም ጊዜ የሚበሉ ሦስት ቀበኞች አሉ፡፡ እነርሱም ኮምፒዩተር፣ ቴሌቪዢንና ከልክ በላይ የሆነ ማኅበራዊ ተሳትፎ(የበዙ ጓደኞችን መጠየቅ፣ ሞባይል ስልክ መደዋወል፣ ማኅበራዊ ኃላፊነቶች፣ እንዲሁም ከልክ ያለፈ አገልግሎት፣ ወዘተ…)፡፡
  - ከትዳር አጋራችን ጋር ያለን ግኑኝነት አካላዊ ብቻ እንዳይሆን እንጠንቀቅ፡፡ ጥልቀት አጥቶ ትርጉም አልባ የሆነ አካላዊ ግኑኝነት አደገኛ ስለሆነ መፈተሽ ያስፈልገዋል፡፡
  - ከትዳር አጋራችን ጋር ያለንን ግኑኝነት ከጓደኞቻችን ወይም ከወላጆቻችን ጋር በመነጋገር ለመተካት አንሞክር፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## እርስ በርስ መግባባት - በባልና በሚስት መካከል *አለመግባባትን የሚያሰፍኑ ምክንያቶች*

- የትዳር አጋራችን እንደማይሰማን/ትሰማን የሚያሳስበን ተስፋ የሚያስቆርጥ ስሜትን ከእኛ እናስወግድ፡፡ ዘወትርም ያለማቋረጥ ስለዚህ ጉዳይ እንጸልይ፡፡ ተገናኝተን መነጋገር ካልቻልን ኤስኤም ኤስ ወይም ኢሜይል እንደራረግ ወይም ሌላ የመግባቢያ ዘዴ እንፈልግ እንጂ አልነጋገርም አንበል፡፡

- እንግዲህ በተጋቢዎች መካከል አለመግባባት፣ አለመነጋገር ወይም አለመገናኘት ካለ ፍቅር አይኖርም፤ የፍቅርም መጥፋት መላውን ትስስር ወይም ትዳር ወደማፍረስ ያደርሳል፡፡
- በተጋቢዎች መካከል ያለ ግኑኝነት በንግግር የሚገለጽ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም እያደግን ስንሄድ በዓይን ወደ መግባባት የሚያደርሰን ነው፡፡
- ፈቃዳችንን ስንፈጽም ከምናደርገው ውጪ እጅ ለጅ የመያያዝ ወይም የመተቃቀፍን አስፈላጊነትን ማውሳትም ለቀባሪ የማርዳት ያህል ነው፡፡
- አበባ ወይም ማንኛውንም አነስተኛ ስጦታ በመስጠት መግባባትንም እንዳንዘነጋው፡፡
- በቃል(ላት) የትዳር አጋራችንን መውደዳችንን ያለማቋረጥ መግለጽ እጅግ አስፈላጊ መሆኑንም አንዘንጋ፡፡ ይህም ስሜታችንንም ሆነ ውስጣችንን በጤናማ ነገር እየመገብን ለማደግ ይረዳናል፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4</u>

## ጣፋጭ ግኑኝነት

- *‹‹ያማረ ቃል የማር ወለላ ነው ለነፍስ ጣፋጭ ለአጥንትም ጤና ነው፡፡›› <u>ምሳ 16፡24፡፡</u>*
- በርካታ ሚስቶች ባሎቻቸው ከጋብቻቸው በፊት ያዘንቡባቸው የነበረውን በርካታ ጣፈጭ ቃላቶችን መጠቀም ማቆማቸውን በተመለከተ ከፍተኛ ምሬታቸውን በመግለጽ ላይ ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ ባሎችም ጣፋጭ ቃሎችን መጠቀምን አስመልክቶ ብቁ ሥልጠና እንዳልወሰዱ ይገልፃሉ፡፡
- ይሁን እንጂ ከትዳር አጋራችን ጋር ጣፋጭ ቃላቶችን መጠቀም ለፍቅር ግኑኝነታችን እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ በጌታችንም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ‹‹ከእናንተ ጋር ቃልን ውሰዱ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተመልሳችሁ፡፡ ኃጢአትን ሁሉ አስወግድ፥ በቸርነትም ተቀበለን፥ በወይፈንም ፋንታ የከንፈራችንን ፍሬ እንሰጣለን፡፡›› *<u>ሆሴ 14፡2፡፡</u>*
- በመጽሐፍ ቅዱስም ‹‹መልካም ቃል›› (ጸሎት) ከማንኛውም ስጦታ ወይም መሥዋዕት በላይ መሆኑ ተገልጦልናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም እነዚህን ቃላት ‹‹እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት፡፡›› *<u>ዕብ 13፡15፡፡</u>* በማለት ይገልጻቸዋል፡፡
- ***እንግዲህ በባልና በሚስት መካከል የሚገኙ ለግኑኝነት የመሆኑ ጣፋጭ ቃላቶች ምንድር ናቸው?***

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## 1. የአክብሮትና የአድናቆት ቃላቶች

- ባሎች ሆይ! ሚስት መልካም ነገር ስታደርግልን የምስጋና ቃላቶችን ብንጠቀም የምንከስረው ምንድር ነው?! ይህ ግዴታዋ ወይም ኃላፊነትዋ እንደሆነ ቆጥረን ከማመስገን እንቆጠባለን?!
- በተቃራኒው ባታደርገው መውቀሳችን ይቀራል?! ታዲያ በሚወቅስ አንደበት ብናደንቅ የሚገባ አይደለምን?!
- ስለዚህ ላደረገችልን ማንኛውም ነገር አድናቆታችንን መግለጣችንና ማክበራችን ከሁሉ ይልቅ ተገቢ አይደለምን?!

## 2. የማበረታቻና የምስጋና ቃላቶች

- በሕይወታችን ዘመን የሠራነው ሥራ የቱንም ያህል ስኬታማ ቢሆን ወይም ዕድሜያችን የቱንም ያህል ቢሆን ሰዎች (ወንድም ሆነ ሴት) ሰዎች አበረታች ቃላትን እንፈልጋለን፡፡ ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ እንመክራችኋለን፤ ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤ ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ፡፡›› *ቀዳ ተሰ 5፡14፡፡* እንዳለ ማጽናት ማበረታትን የማንፈልግ የለንም፡፡
- የማጽናት ወይም የማበረታቻና የምስጋና ቃላት መኪና ጋብቻን (ትዳርን) ያለማቋረጥ ጉዞውን እንዲቀጥል የሚያደርጉ ነዳጅ ናቸው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## 3. የፍቅር ቃላት

- አንዳንዶች ፍቅርን ለትዳር አጋር የመግለጽን አስፈላጊነት የሚቀበሉና የሚከተሉት ቢሆንም ሌሎች ደግሞ የፍቅር ቃላትን ተጠቅመው የማያውቁ መሆኑን ይገልጣሉ፡፡
- ማንኛውም ልማድ ተደጋግሞ ሲፈጸም ቆይቶ ተዋህዶን የሚቀር መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ከሌሊቱ በ11 ሰዓት የምንነሳበት አዲስ ሥራ ብንጀምር ከሥራው ሰዓት አስቀድሞ መነሳትን መለማመድ ያስፈልገናል፡፡
- ስንጀምረው አስቀድመን ካለማድረጋችን የተነሳ ቢከብደንም ደጋግመን ስንለማመደው ሥራ በማይኖርበትም ቀን ሳይቀር በ11 ሰዓት የምንነቃበትን ልምድ እናዳብራለን፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር ለሰጠን የትዳር አጋራችን ፍቅራችንን መግለጽን መማር አያስፈልገንም ይሆን!!!
- የትዳር አጋራችንን እንደምንወድ ስለምን አንገልጽም? ምን ያህል እንደምንወድ ስለምን አንናገርም? እርሱን/ስዋን የሰጠ እግዚአብሔርን ምን ያህል እንደምናመሰግን ስለምን አንናገርም? ምን ያህል እንደምንኮራበት/ባት፣ እንደምናምነው/ናት፣ እንደምንተማመንበት/ባት ስለምን አንናገርም?

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## 4. የጸሎት ቃላት

- ‹‹እግዚአብሔር በረከቱም ያብዛልሽ፣ እግዚአብሔር ልብሽን በደስታ በሐሴት ይሙላ፣ እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሽ፣ እግዚአብሔር ስኬትን ሁሉ ይስጥሽ…›› የሚሉ ቃላትን መጠቀም በተጋቢዎች መካከል ያለውን ግኑኝነት ከማጥበቁም በላይ እግዚአብሔርን ስለ ግኑኝነታችን ቀጣይነት በመካከላችን እንዲኖር ይጋብዙታል፡፡

## 5. የይቅርታ ቃላት

- በጥፋተኝነት ስሜት በወቅቱ የሚቀርብ የይቅርታ ቃል ምን ያህል ታላቅ ነው…
- ስህተታችንን ተቀብለን ‹‹ተሳስቻለሁ… አዝናለሁ… እባክህ/ሽ አትናደድብኝ/ጅብኝ… ስህተት መፈጸሜን አውቄዋለሁ… ነገር ግን ደግሜ ላለመፈጸም እጠነቀቃለሁ… ይቅር እንድትለኝ/ይኝ ምን ላድርግ?… አሁን ላስደስትህ/ትሽ የምችለው በምንድር ነው?!!! ….›› ስንል ምን ያህል ድንቅ ነው፡፡

## 6. ጤናማ ተግሳጽ ያለባቸው ቃላት

- ላደረገው/ገችው ነገር ጠንከር ያለ ተግሳጽ ማቅረብ ሁልጊዜ ስህተት ሊሆን አይችልም፡፡
- ጤናማ አቀራረብ ያለው ተግሳጽ የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ከመሆኑም በላይ ጣፋጭም ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 4

6. ጤናማ ተግሳጽ ያለባቸው ቃላት

- ይሁን እንጂ ይህ ጉዳይ ተግሳጽን በፍቅር የማቅረብ ችሎታን ወይም ጥበብን ይፈልጋል። ወቀሳ የሚያቀርብ ወይም የሚገስጽ ሰው በይቅርታ መጀመር አለበት፤ በማስከተልም የተሠሩ ስህተቶችን በተመረጡ ቃላት ማስተላለፍ ይገባዋል።
- በማጠቃለያውም በትሕትና በፍጹም እርጋታና ፈገግታ ሆነን ጉዳዩን ማስረዳት ይኖርብናል።
- ይህን ካደረግን ከትዳር አጋራችን ጋር በመሸናነፍ መንፈስ ሆነን ችግሩን ፈተን እናልፋለን።

7. የጽሑፍ መልዕክት

- የተወደዳችሁ ባሎች ሆይ! ሚስቶች ዝም ብለው ደብዳቤዎችን፣ ኢሜይሎችን፣ መልዕክቶችን፣ ካርዶችን፣ ወዘተ መቀበል እንደሚወዱ ታውቃላችሁ። እያንዳንዱ ወደ ትዳር አጋራችን የምንልከው ገላጭ የሆነ የኤስኤምኤስ መልዕክት ከፍተኛ ጤናማ ለውጥን የማምጣት አቅም አለው። ስለዚህ በዚህ ፈጣን ዘዴ ስንጠቀም የትዳር ጥበበኞች እንሁን።

8. የመሻትና የመናፈቅ ቃላት

- አንዳንዶች የትዳር አጋራቸውን መናፈቃቸውን ወይም መሻታቸውን መግለጽ ያሳፍራቸዋል። ‹‹ታስፈልገኛለህ/ጊኛለሽ፣ ስሜቴን እንድትጋራኝ/ጋሪኝ፣ እንድትሰማኝ/ሚኝ እፈልጋለሁ...›› ማለትን አይደፍሩም።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4

## 8. የመሻትና የመናፈቅ ቃላት

- እውነታው ግን እነዚህን ቃላት በተጠቀምን ቁጥር የትዳር አጋራችን ምን ያህል ለሕይወታችን አስፈላጊ እንደሆነ/ች ከማረጋገጣችንም በላይ ማንኛውንም ስሜታችንን፣ ፍላጎታችንንና፣ ሐዘናችንን ሁሉ ዘወትር እንድናካፍል መርዳቱ ነው፡፡
- ጌታችን ውሃ በተጠማ ጊዜ ‹‹ውሃ ስጪኝ›› *ዮሐ 4፡7፡፡* በማለት ጠይቋል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስንም ‹‹የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?›› *ዮሐ 21፡15* ብሎታል፡፡

## 9. ሞቅታ ያለው መነካካት

- በትዳር ሕይወት ሞቅ ያለ መነካካት የሞተን አካል በኤሌክትሪክ ንዝረት እንደመቀስቀስ ነው፡፡ እጃችንን በትዳር አጋራችን ትከሻ ላይ ማሳረፍ፣ ወደርሱ/ስዋ በአድናቆት መመልከት፣ ማቀፍም ሆነ መሳም በባለትዳሮች መካከል ሊኖር የሚገባው የመግባቢያ ዘዴ ነው፡፡
- ጌታችን አምላካችን ‹‹ለምጻሙን … ኢየሱስም አዘነለት እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፡፡ እወድዳለሁ፤ ንጻ አለው፡፡›› *ማር 1፡41፡፡* ‹‹ሕፃናትን … አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው፡፡›› *ማር 10፡16፡፡* እንደተባለ በፍቅር በሆነ መንካት ርኅራኄን እንዳስተማረን እንረዳ፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 4</u>

9. **ሞቅታ ያለው መነካካት**

- ተወዳጆች ሆይ! በመጨረሻም የወቀሳን… የነቀፋን… የስድብን… የመፎካከርን… የትዕቢት… የቁጣ ቃላትን ከመጠቀም እንቆጠብ፡፡ መጽሐፍም ‹‹የጎጥኣን ቤት ይፈርሳል የቅኖች ማደሪያ ግን ያብባል፡፡›› *<u>ምሳ 13፡11</u>*፣ ‹‹ሙሽራዬ ሆይ፥ ከከንፈሮችሽ ማር ይንጠበጠባል ከምላስሽ በታች ማርና ወተት አለ፥ የልብስሽም መዓዛ እንደ ሊባኖስ ሽታ ነው፡፡›› *<u>መኃ 4፡11፡፡</u>* ያለንን እናስተውል - ልብ እንበል!፡፡

## *መነጋገር የመግባቢያ መንገድ ነው፡፡*

- በትዳር አጋሮች መካከል የጋራ መረዳዳት የሚጎድልበት አንዱ ምክንያት አለመግባባት ወይም ጤናማ ያለሆነ ግኑኝነት ሲሆን በዚህ የተነሳ በትዳሩ ለሚፈጠር ግጭት ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
- ስለዚህ በትዳር አጋራችን ልቦናና አእምሮ የሚመላለሰውን በመረዳት በተገለጠው ጠባዩ/ይዋ የታየውን ያመጣው ምን እንደሆነ ለማወቅ እንጣጣር፡፡
- ይህንም ለይቶ ማወቅ የትዳር አጋራችንን ስሜታዊና ሥነ ልቦናዊ ፍላጎት ሕልምና እደርስበታለሁ ያሉበትን ሁሉ ለይተን በማወቅ በሚፈለገው እንድንካፈላቸው ይረዳናል፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org